# <u>ዛሬ ነገ አንበል!</u> (ግጥም)

(ከወጣት ሰላማዊት ጌታነህ)

“ፍትህ ነፃነት ዴሞክራሲ የህግ በላይነት
ይከበር ይተግበር በላዕላይነት”

ብላ በተነሳች ለማስከበር የህዝቦች ነፃነት
የወያኔ ሰዎች ካላግባብ ነፃነትን ገፈውባት
ሰብአዊ መብቶችዋን ረግጠውባት
ቀኖችም አልፈው ሲቆጠሩ ወራት
በዚያ በጨለማው በቆርቆሮ እስርቤት።

ወገኔ!!!
ምን ዋጋ አለው ትርጉም አልባ ኑሮ
ፍትህ ላይገኝበት መንገላታት በቀጠሮ

ዛሬ ነገ አንበል ሆ!! ብለን እንነሳ
ለፍትህ ነጻነት እጃችህን አንሳ

ሀገር ስትደፈር ህዝብህ ሲንገላታ
ነጻነቱን አጥቶ በፍርድ አረንቃ ሲመታ

እስቲ እናቅርብ ጥያቄያችንን ለአምላካችን
እውነተኛውን የማያዳላውን ፍርድ እንዲሰጠን
ከእስር ቤት አውጥቶ ለትግል እንዲያበቃልን
ብርቅየዋ ብርቱካንን የትግል መሪያችንን

አይሟሽሽ ወኔያችን አይተኛ ልባችን
ፍትህ ና ነፃነት እንዲከበር በሀገራችን
በርትተን እንስራ በጋራ ሁላችን።

---
ወጣት ሰላማዊት በሲያትል የአንድነት ድጋፍ
ስራ-አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል ናት።